# ስምንተኛ ፡ የዲኑ ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫ ፤ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም.


በክሊፍ ፡ ቶምሰን ፤ ፕሮፌሰርና ፡ ዲን ፤

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡

የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ።


አንድ ፡ አዲስ ፡ ዲን ፡ ተቀባይነት ፡ ያለው ፡ የሕሊና ፡ ግምት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ ያሁኑን ፡ ሁናቴዎች ፡ ታሪካዊ ፡ አቅጣጫ ፡ እንዲይዙ ፡ በማድረግ ፡ ነው ። ባለፈው ፡ ዓመት ፡ በሰጠሁት ፡ መግለጫዬ ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ መሸጋገሪያ ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ እንደሆነ ፡ ገልጬ ፡ ነበር ። እኔ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ያየሁት ፡ መጀመሪያ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ በውጭ ፡ ዜጎች ፡ መምህራን ፡ ተሞልቶና አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ከነበረበት ፡ ተለውጦ ፡ ቋሚና ፡ አብዛኞቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ፡ ሆኖ ፡ ነው ።

ነገሩ ፡ ለወደፊት ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አቅጣጫ ፡ ይቀጥላል ። መሸጋገሪያ ፡ ጊዜ ፡ በተባለው ፡ አነጋገር ፡ ውስጥ ፡ ታዝለው ፡ የሚገኙት ፡ ነገሮች ፡ በየዓመቱ ፡ ለወደፊት ፡ በሚደረጉት ፡ መግለጫዎች ፡ ውስጥ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ በብዛት ፡ ይገኙባቸዋል ።

ቢሆንም ፡ የዚህ ፡ ዓመት ፡ መግለጫዬ ፡ በጣም ፡ አትኩሮ ፡ የሚመለከተው ፡ የተጀመሩትን ፡ ወይም ፡ ያለቁትን ፡ ሥራዎች ይሆንና ፡ ፋክልቲው ፡ ከለጋነት ፡ ወደ ፡ መደርጀት ፡ በሚተላለፍበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚታዩት ፡ ነገሮች ፡ አስተያየት ፡ መስጠት ፡ ለሚመጣ ፡ ዓመት ፡ እንዲሆን ፡ አስተላልፌዋለሁ ።

## ሀ. ያልተለመዱ ፡ ክንውኖችና ፡ ድርጊቶች ።

መጀመሪያ ፡ ልጠቅሰው ፡ የምወደው ፡ የሕግ ፤ ት/ቤት ፡ ከተለመደውና ፡ ከሚፈለግበት ፡ መሻሻል ፡ በላይ ፡ እንዲያደርግ ፡ ሊያደርጉ ፡ የቻሉትን ፡ እያሌ ፡ ያመቱ ፡ ክንውኖች ፡ ናቸው ። ይህንንም ፡ ስል ፡ «ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ ለኛ ፡ የተለመደ ፡ ነው ፡ ለሚለው ፡ አባባል ፡ ፋክልቲያችን ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ እንዳለው ፡ ላሳስብ ፡ እፈልጋለሁ ። ባለፉት ፡ ስምንት ፡ ዓመታት ፡ ፕሮግራሞች ፡ የማውጣት ፡ ችሎታችን ፡ በሚያስደንቅ ፡ እኳኋን ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ።

### እንተርናሽናል ፡ (ዓለም ፡ አቀፍ) ፡ ጂሳፕ ፡ የመለማመጃ ፡ ክርክር ፡ ውድድር ፡

የእንተርናሽናል ፡ ጂሳፕ ፡ የመለማመጃ ፡ ክርክር ፡ ውድድር ፡ የኛን ፡ ፋካልቲ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ አፍሪቃን ፡ ወክሎ ፡ በዋሽንግተን ፡ ዲ. ሲ. በተደረገው ፡ ውድድር ፡ እንዲካፈል ፡ መርጦት ፡ ነበር ። ይህ ፡ ፕሮግራም ፡ ባመቱ ፡ ከተከናወኑት ፡ የቀለም ፡ ትምህርት ፡ ከሆኑትና ፡ ካልሆኑት ፡ ነገሮች ፤ ያላንዳች ፡ ጥርጥር ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ የሚይዝ ፡ ነበር ። ለዚህ ፡ ውድድር ፡ ወደ ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ የሚሆኑት ፡ ተማሪዎች ፡ ንቃት ፡ በተሞላ ፡ እኳኋን ፡ ተካፋዮች ፡ ከሆኑት ፡ ውስጥ ፡ ሐጎስ ፡ ሃይሌና ፡ የወንድወሰን ፡ መክብብ ፡ እንዲሁም ፡ በተጠባባቂነት ፡ በዛወርቅ ፡ ሺመላሽ ፡ የኛን ፡ ቡድን ፡ ወካዮች ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ። የመጨረሻ ፡ መረጣ ፡ የተደረገው ፡ በሕግ ፡ ተማሪዎች፡

መኝታ ፡ ቤት ፡ አዳራሽ ፡ በተከናወኑት ፡ በሁለት ፡ የመለማመጃ ፡ ክርክር ፡ ውድድሮች ፡ ሲሆን ፡ የተፈረደውም ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በሁለቱም ፡ ጊዜ ፡ ተጠርተው ፡ በነበሩት ፡ የታወቁ ፡ ዘጠኝ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ በሆኑት ፡ ዳኞች ፡ ነው ። ከባዱ ፡ ሥራ ፡ ዋጋውን ፡ አስገኝቷል ። የተወዳዳሪዎች ፡ ችሎታ ፡ ስሜቶቻችንን ፡ እንዲረኩ ፡ አድርጓል ። ስለዚህም ፡ ጉዳዩ ፡ ከሚሰጡት ፡ አስደሳች ፡ አስተያየቶች ፡ ካላለፉት ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ አንዱ ፡ ተማሪ ፡ የሰነዘረው ፡ ስለችሎታቸው ፡ በቀላሉ ፡ ያስረዳል ፤ እርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፤ «በውነቱ ፡ እነርሱ ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ ከነበርንበት ፡ ረጅም ፡ መንገድ ፡ መጥተዋል» ።

የውድድሩ ፡ ዋና ፡ ጠቃሚነት ፡ ያለው ፡ እስከዚህም ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ሕግ ፡ ስላለበት ፡ ሳይሆን ፡ ሕግ ፡ ጠቀስ ፡ የሆኑትን ፡ ጥያቄዎች ፡ የማየትና ፡ በነርሱም ፡ በደንብ ፡ ለመከራከር ፡ የሚያስችለውን ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎችን ፡ ችሎታ ፡ ለማግኘት ፡ የተደረገው  ሙከራ ፡ ነው ። በውድድሩ ፡ ጊዜ ፡ የተሰየሙት ፡ ዳኞች ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የቀረበ ፡ ንግግር ፡ እንዲያደርጉ ፡ አልፈቀዱላቸውም ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ዳኞቹ ፡ ከባድ ፡ ጥያቄዎችን ፡ እየጠየቁ ፡ ተናጋሪዎቹን ፡ ፋታ ፡ በከለከሏቸው ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሁሉም ፡ ተወዳዳሪዎቻችን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ችሎታቸው ፡ እየጨመረ ፡ ከመሄዱ ፡ የተነሣ ፡ ለሁሉም ፡ ተማሪዎች ፡ ሊዳረስ ፡ የሚችለውን ፡ አጠቃላይና ፡ ውጤት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችል ፡ የመለማመጃ ፡ ክርክር ፡ ውድድር ፡ ፕሮግራም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ ችለናል ።

በዋሽንግተን ፡ ዲ.ሲ. የእኛ ፡ ተማሪዎች ፡ በቀጥታ ፡ ለመጨረሻ ፡ ዙር ፡ በሚያሳልፈው ፡ ውድድር ፡ ገቡና ፡ ያኔውኑ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ በጥሎ ፡ ማለፍ ፡ ውድድር ፡ አሸናፊዎች ፡ ከሆኑ ፡ ቡድኖች ፡ ጋር ፡ ተወዳደሩ ። ስለቡድናችን ፡ ብዙ ፡ መግለጫዎች ፡ ተላልፈውልን ፡ ነበር ፤ በሁሉም ፡ ቡድናችን ፡ በጣም ፡ ጉበዝ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ቃል ፡ ይገኝባቸዋል ። የተሰየሙት ፡ ዳኞች ፡ ምርጫ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የኛ ፡ ቡድን ፡ ያበቃው ፡ ከዘጠኙ ፡ ለመጨረሻ ፡ ጥሎ ፡ ማለፍ ፡ ውድድር ፡ ከሚያደርጉት ፡ ቡድኖች ፡ መካከል ፡ ላይ ፡ ነበር ። በጣም ፡ ስሜት ፡ የሚያረካው ፡ የተሰየሙት ፡ ዳኞች ፡ በውድድሩ ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ላሳየው ፡ ተናጋሪ ፡ ምርጫ ፡ ሲያደርጉ ፡ ሐጐስ ፡ ኃይሉ ፡ የስድስተኛነት ፡ የወንድ ፡ ወሰን ፡ መክብብ ፡ የሦስተኛነት ፡ ማዕረግ ፡ ማግኘታቸው ፡ ነው ።

በፋክልቲያችን ፡ ይህንን ፡ ውድድር ፡ ያዘጋጁት ፡ ተባባሪ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሮን ፡ ስክላር ፡ ቢሆኑም ፡ አብዛኞቹ ፡ መምህራን ፡ በመፍረድና ፡ ሐሳብ ፡ በመስጠት ፡ ረድተዋል ። ውጤቱ ፡ ሁላችንን ፡ የሚያስደስተንና ፡ የሚያኮራን ፡ ነው ።

<u>በኢትዮጵያ ፡ ስለሕግ ፡ አዋቂዎችና ፡ ስለሕግ ፡ ትምህርት ፡ ጉዳይ ፡ የተደረገው ፡ ስብሰባ ።</u>

የፍርድ ፡ አስተዳደር ፡ ሃላፊነት ፡ ያላቸው ፡ የመንግሥት ፡ የበላይ ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፤ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ አባሎችና ፡ ጥቂት ፡ በጣም ፡ የታወቁት ፡ የግል ፡ ጠበቆች ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ለሁለት ፡ ቀናት ፡ ያህል ፡ በገሊላ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተሰብስበው ፡ ሁላቸውንም ፡ በሚመለከቱት ፡ ነገሮች ፡ ላይ  ከመወያየታቸው ፡ በላይ ፡ ተከራክረውበታል ።

ከዚህ ፡ ተመርቀው ፡ የሚወጡትንና ፡ ለአገሪቱ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል ፡ ተብሎ ፡ የታሰበው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎትን ፡ በሚገባ ፡ ለመጠቀምና ፡ ለመቅጠር ፡ እንዴት ፡ እንደሚቻል ፡ ፍሬያማ ፡ ውይይት ፡ ከመደረጉም ፡ ሌላ ፡ ለምርምር ፡ ጥናት ፡ የሚሰጠው ፡ ቀደምትነት ፡ ምን ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ተወስኗል ። የዚህ ፡ ዓይ

ነቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ስብሰባ ፡ ያዘጋጁት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቢ.ጂ. ቴኔሪ ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ፡ ያገኙት ፡ ከኤ.አይ.ዲ. (AID) ድርጅት ፡ ነው ፤ እርሳቸውም ፡ ለወደፊት ፡ ለሚደረጉ ፡ ውይይቶች ፡ የሚሆን ፡ መግለጫ ፡ አዘጋጅተዋል ።

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስካሁን ፡ ፋኩልቲው፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ዕድገት ፡ እውነተኛ ፡ ችግሮች ፡ የሆኑትን ፡ ለማወቅ ፡ በድርጅት፡ ለምሳሌ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቦርድ ፡ በኩልና ፡ በሌላም ፡ ባልተገለጹ ፡ መንገዶች ፡ ግንኙነቱን ፡ ጠብቆ ፡ ቆይቷል ። ስብሰባው ፡ ሥርዓታዊ ፡ (Systematic) መሻሻል ፡ እንዲኖር ፡ ከሚደረጉት ፡ ጥረቶች ፡ ማለት ፡ የሥራ ፡ ልምምድና ፡ የቀለም ፡ ትምህርት ፡ ጉትት ፡ እንዲደራረቡ ፡ ወይም ፡ አብረው ፡ እንዲሄዱ ፡ ለማድረግ ፡ ሊቋቋም ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ድርጅት ፡ አንዱ ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡ ይህንኑ ፡ ዓላማ ፡ የሚያሳየው፡ የአማርኛ ፡ የእንግሊዝኛና ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ የያዘ ፡ የሥርዓተ ፡ ቃላት ፡ መጽሐፍ ፡ በደንብ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በፋክልቲው ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ መውጣቱ ፡ ነው ።

## የአማርኛ ፡ የእንግሊዝኛና ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ሥርዓተ ፡ ቃላት ፡ መጽሐፍ ።

ለዘመናዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ የሆኑት ፡ በአማርኛ ፡ በእንግሊዝኛና ፡ በፈረንሳይኛ ፡ በተጻፉት ፡ የሕግ ፡ መማሪያ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ሕግ ፡ ጠቀስ ፡ የሆኑ ፡ ሐረጎችን ፡ በሥርዓተ ፡ ቃላት ፡ መልክ ፡ በሦስቱም ፡ ቋንቋ ፡ መጽሐፍ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ከተጀመረ ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ሆኖታል ።

የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ የብሔራዊ ፡ የሕግ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲፈጠር ለማፋጠንና ፡ ምክንያቱንም ፡ ለማስረዳት ፡ እንደሆነ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ «ሞርትጌጅ» ፡ (Mortgage) የሚለው ፡ ቃል ፡ በተለያዩ ፡ አማርኛ ፡ ትርጓሜዎች ፡ ውስጥ ፡ የተለያየ ፡ አባባል ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ፋኩልቲው፡ ከእንግሊዝኛ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎችንና ፡ መጽሐፎች ፡ የተረጐማቸው ፡ ሕግ ፡ ጠቀስ ፡ ያማርኛ ፡ ቃላት ፡ የበለጠ ፡ ብዛት ፡ ሰጥቶታል ።

ከፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ የተላኩት ፡ በጐ ፡ ፈቃደኛ ፡ ሚስትር ፡ ጃክ ፡ ቡሩ ፡ ሦስቱንም ፡ ቋንቋዎች ፡ የሚችሉ ፡ ስለሆኑ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ መጽሐፍ፡ የመጀመሪያውን ፡ እትም ፡ ጨረሱ ። የርሳቸውም ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ በሦስቱም ፡ ቋንቋዎች ፡ ምን ፡ እንደሚባል ፡ ለማወቅ ፡ ያስችላል ። መጽሐፉ ፡ ተባዝቶ ፡ ለተለያዩ ፡ የሥራ ክፍሎች ፡ ወይም ፡ በነገሩ ፡ ልዩ ፡ ስሜት ፡ ለሚያሳዩ ፡ ሰዎች ፡ ለምሳሌ ፡ በዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ ለአማርኛ ፡ ትምህርትን ፡ ጥናት ፡ ክፍል ፡ (Amharic Department) እንዲሁም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሽልማት ፡ ድርጅት ፡ ላሉት ፡ ለዶክተር ፡ ብርሃኑ ፡ አበበ ፡ በመታደል ፡ ላይ ፡ ነው ።

ከመጀመሪያው ፡ እትም ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ለማለፍ ፡ የምንችለው ፡ በሕግ ፡ መጻሕፍት፡ (Codes) ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ሕግ ፡ ጠቀስ ፡ የሆኑ ፡ ሐረጐችን ፡ ያሉበትን ፡ ሊያሳይ፡ የሚችል ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ሰንጠረዥ ፡ (Indexing) ስንጨርስና ፡ የአማርኛ ፡ ሐረጐች ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ለማሳጠር ፡ ሙከራ ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ እንደኔ ፡ ሐሳብ ፡ ከሆነ ፡ የሚቀጥለው ፡ ሥራ ፡ ማትኮር ፡ ያለበት ፡ በሕግ ፡ ሙያ ፡ (ሥራ) ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ቃላትና ፡ ሐረጐች ፡ ለጉዳዩ ፡ የሚያገለግሉትን፡ እንዲመርጡ ፡ ማድረግና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በነዚያ ፡ ሕግ ፡ ጠቀስ ፡ የሆነ ፡ የሥርዓት ፡ ቃላት ፡ መጽሐፍ ፡ ማዘጋጀት ፡ ነው ። ብሔራዊ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ ቋንቋ ፡ በጥናት ፡ እንዲያድግ ፡ ሲፈለግ ፡ ሥራው ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሚጠይቅና ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ከመጀመሪያው ፡ ወይም ፡ አሁኑኑ ፡ በሥራ ፡ ለማዋል ፡ ኀይለኛ ፡ ልምምድ ፡ መደረግ ፡

አለበት ። በዚህ ፡ አጋጣሚ ፤ የንግድ ፡ ትምህርት ፡ ነክ ፡ የሆኑትን ፡ የአማርኛና ፡ የእን ግሊዝኛ ፡ ሐረጐችን ፡ ግልጽና ፡ ጠቃሚ ፡ ሕግ ፡ ጠቀስ ፡ የሆኑ ፡ የአማርኛ ፡ አሳቦች ፡ እንዲያድጉ ፡ ለመርዳት ፡ ሲሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትጋት ፡ ያሳዩትን ፡ ፔተር ፡ ዊንሽፕን ፡ መጥ ቀስ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

## <u>በኖርዝዌስተርንና ፡ በቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርስቲ ፡ ሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ መካከል ፡ የሚደ ረገው ፡ የጥናት ፡ ውጥን ፤</u>

ውጥኑ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ የሚፈጅ ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ የመስክ ፡ ሥራ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሲሆን ፡ ጥናቱም ፡ የሚያተኩረው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጠቃሚ ፡ ናቸው ፡ በተባሉት ፡ ነገሮች፡ ላይ ፡ ነው ። ለፋክልቲው ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ውጥን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የአምናው ፡ እ.ኤ.አ. ከ፲፱፻፷፰—፲፱፻፸፬ ዓ.ም. አንሥቶ ፡ እስካሁን ፡ የሁለ ተኛ ፡ሙከራ ፡ ነው ። እኛም ፡ ተማሪዎቻችንን ፡ በጥናቱና ፡ በምርምር ፡ ጽሑፎች ፡ እን ዲካፈሉ ፡ አድርገናል ።

እንደዚሁም ፡ በችሎታቸው ፡ በታወቁት ፡ በተባባሪ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቤክስትሮም ፡ የተመራው ፡ የውጥኑ ፡ ቡድኖች ፡ የተወጣጡት ፡ ሦስት ፡ ከኖርዝዌስተረን ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ሦስት ፡ ተማሪዎች ፡ ከኛ ፡ ፋክልቲ ፡ ሲሆኑ ፡ አያሌ ፡ አጥኚዎች ፡ ተማ ሪዎች ፡ ከማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሥራ ፡ ትምህርት ፡ ቤትና ፡ ከኛ ፡ ፋክልቲ ፡ ነው ። ጥናቱ ፡ ተደጋጋሚ ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ (interdisciplinary) እውነቱ ፡ ለማግኘት ፡ የሚደረ ገው ፡ ሙከራ ፡ ቢሆንም ፡ የሚያተኩርው ፡ የተቸገሩ ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ ወጣቶች ፡ በሕ ብረሰብ ፤ በኤኮኖሚ ፡ በአገዛዝ ፡ ወይም ፡ በፖለቲካና ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ምን ፡ ሊያስከ ትሉ ፡ እንደሚችሉና ፤ በመርካቶ ፡ የሚገኙት ፡ ባሕላዊ ፡ የሆኑ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ በኤኮኖሚ ፡ ለወደፊት ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉት ፡ ጥቅምና ፡ ሊያስከትሉ ፡ የሚችሉት ፡ችግ ሮች ፡ የትኞቹ ፡ እንደሆኑ ፡ ለመለየት ፡ ነው ።

የመጀመሪያው ፡ የኖርዝዌስተረንና ፡ የቀ.ኃ ሥ ዩኒቨርስቲ ፡ ውጥን ፡ ሦስት ፡ የም ርምር ፡ ጽሑፎች ፡ እንዲታተሙ ፡ ያደረገ ፡ ስለሆነ ፡ ባሁኑም ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ውጤት እንደሚያስገኝ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፡ ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ አብዛኛውን፡ ጊዜ ፡ አከራካሪና ፡ የተወሳሰቡ ፡ በሆኑ ፡ በመስክ ፡ ሥራ ፡ ጥናት ፡ የቅርብ ፡ ተቈጣጣሪነ ትና ፡ ግንኙነት ፡ ከማድረጋቸው ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ጥቅሞች ፡ ለማግኘት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ አጋጥሟቸዋል ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ።

## <u>በአፍሪቃ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብቶች ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ የአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ ዕድገት፡ ድርጅት ፡ ለአፍሪቃ ፡ ኤኮኖሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ ያደረገው ፡ ስጦታ፤</u>

እ.ኤ.አ. ፲፱፻፸፩ ዓ.ም. በፀደይ ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ የአፍሪቃ ፡ የኤኮኖሚክ ፡ ኮሚ ሽን ፡ በአፍሪቃ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብቶች ፡ የሚመለከት ፡ አንድ ፡ ስብሰባ ፡ አዘጋጅ ፡ ነበር ። በስብሰባው ፡ ወቅት ፡ በኒዮርክ ፡ የሚገኘውና ፡ በፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ የሚረ ዳው ፡ የኢንተርናሽናል ፡ (ዓለም ፡ አቀፍ) ፡ የሕግ ፡ ድርጅት ፡ የጉዞና ፡ ሌላም ፡ ድጋፍ ፡ ሲሰጥ ፡ በኛ ፡ ፋክልቲ ፡ የሚገኘው ፡ የአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ ዕድገት ፡ ድርጅት ፡ ታሪካዊና ፡ ጠቃሚ ፡ ጽሑፎች ፡ በማበርከት ፡ ረድቷል ። የእርዳታውን ፡ ዝግጅት ፡ ያደ ረጉት ፡ ዶክተር ፡ ቲየሪ ፡ ቨርሃልስት ፡ የአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ ድርጅት ፡ ሁለተኛ ፡ ዲሬክተር ፡ ናቸው ፤ ከተሰጡት ፡ ጠቃሚ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ የፕሮፌሰር ፡ አን ፡ ሚሪ ፡ ሚሌትና ፡ የሚስተር ፡ ዚግመንት ፡ ፕላተር ፡ ሥራዎች ፡ ይገኙባቸዋል ።

በስብሰባው ፡ ሳቢያ ፡ የአፍሪቃ ፡ ሕግ ፡ ዕድገት ፡ ድርጅት ፡ ሊያደርግ ፡ የሚችለውን ፡ ያህል ፤ እርዳታ ፡ ሰጥቶ ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ስለድርጅቱ ፡ በፕሮፌሰር ፡ ጃክ ፡ ቫንደርልንደን ፡ ታስቦ ፡ የነበረው ፡ የመጀመሪያ ፡ አስተሳሰብ ፡ ማለት ፡ ድርጅቱ ፡ በመሠረቱ ፡ አፍሪቃዊ ፡ የሆነ ፡ የአፍሪቃ ፡ ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ ወይም፡ማጠራቀሚያ ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ የተገለጸውን ፡ ስለምናምን ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የስብሰባው ፡ ተወካዮች ፡ በአፍሪቃ ፡ አንጻር ፡ « የአምቡድስማን ፡ » ፅንስሐሳብ ፡ (Concept ) ምን ፡ ያህል ፡ ዕድገት ፡ እንዳሳየ ፡ ለማወቅ ፡ ልዩ ፡ ስሜት ፡ ባሳዩ ፡ ጊዜ ፡ ድርጅቱ ፡ በሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ ለሁሉም ፡ ተወካዮች ፡ ስለጉዳዩ ፡ ጠቀስ ፡ የሆኑ ፡ ድንጋጌ ፡ (ሕግ) ሊያድል ፡ ችሎ ፡ ነበር ።

በስብሰባው ፡ ጊዜ ፡ የኛ ፡ ድርጅት ፡ በስብሰባው ፡ ውስጥ ፡ በመገኘት ፡ መግለጫ ፡ ሰጪ ፡ (Rapporteur) እንዲሆን ፡ በአፍሪቃ ፡ ኤኮኖሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በመጠየቁ ፡ ለድርጅታችን ፡ ትልቅ ፡ ዋጋ ፡ መሆኑን ፡ እምናለሁ ። በስብሰባው ፡ ውስጥ፡ የተካሄዱት ፡ ነገሮች ፡ ከመሠረታዊ ፡ (Back Ground) ጽሑፎችና ፡ ከተመረጡ ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንዲሁም ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ የተገኙበትን ፡ ከሚያሳይ ፡ መግለጫ ፡ (Bibliography) ጋር ፡ ድርጅቱ ፡ አትሞ ፡ ያወጣል ።

## በኢትዮጵያና ፡ በሱዳን ፡ መካከል ፡ የሚደረገው ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ የመለዋወጥ ፡ ፕሮግራም ።

ከአምስት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ መለዋወጥ ፡ በኛና ፡ በካርቱም ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ መካከል ፡ ነበር ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ ሊቀር ፡ የቻለው ፡ ሐሳቡ ፡ ዋጋቢስ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ስላልሆነ ፡ በዲን ፡ ሳይድ ፡ መሐመድ ፡ አህመድ ፡ ኤል ፡ ማህዲና ፡ በኔ ፡ መካከል ፡ ነገሩን ፡ እንደገና ፡ ለመጀመር ፡ ብዙ ፡ ግንኙነት ፡ በማድረግ ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ ተለዋውጠን ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የካርቱም ፡ ዩኑቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ተማሪ ፡ አህመድ ፡ ኤል ፡ ቃሲም ፡ ጎብኚ ፡ ሆኖ ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፸—፸፩ ዓ. ም. በሁለተኛ ፡ የትምህርት ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ፋኩልቲያችን ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ መጀመሪያ ፡ የተማሪዎች ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ አይቶ ፡ ቢማረርም ፤ እንደምንም ፡ ተስማምቶ ፡ ጓደኞች ፡ በማግኘት ፡ በቀለም ፡ ትምህርትና ፡ በሕብረሰብ ፡ ኑሮ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኗል ።

የመለዋወጡ ፡ ፕሮግራም ፡ ዓላማ ፡ ጐብኞቹ ፡ ተማሪዎች ፡ ከአገራቸው ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ የባሕልና ፡ ሌሎችም ፡ ልዩነቶች ፡ ከማወቅ ፡ የሚያገኙት ፡ ጥቅም ፡ ነው ። ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ተስፋ ፡ የሚደረግበት ፡ ዓላማ ፡ በሁለቱ ፡ ጐረቤት ፡ አገሮች ፡ ማለት ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሱዳን ፡ መካከል ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ በቆየ ፡ የጠበቀ ፡ ወዳጅነት ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ በትንሹ ፡ ለመጨመር ፡ ነው ። የመለዋወጡ ፡ ፕሮግራም ፡ ሲቀጥል ፡ ብዙ ፡ የመጐብኘት ፡ ዕድል ፡ የደረሳቸው ፡ የሕግ ፡ ምርቆች ፡ ሲገኙና ፡ ከነዚህም ፡ አብዛኞቹ ፡ ለአገሪቱ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆኑትን ፡ ቦታዎች ፡ የሚይዙ ፡ ስለሆኑ ፡ ጎረቤት ፡ አገራቸውን ፡ እንደአዲስ ፡ አገር ፡ በመመልከት ፡ ፈንታ ፡ የጓደኞችና ፡ የወዳጆች ፡ አገር ፡ አድርገው ፡ ያዩታል ።

## የተለየ ፡ ተከታታይ ፡ ንግግር ።

የአፍሪቃ ፡ ሕግ ፡ ዕድገት ፡ ድርጅት ፤ የምርምር ፡ ጥናትና ፡ የሕትሞች ፡ ኮሚቴና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ የተለዩ ፡ ተከታታይ ፡ የሆኑ ፡ ንግግሮች ፡ አዘጋጅተው ፡ ነበር ። በፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ በተደረገው ፡ እርዳታ ፡ ምክንያት ፡ የፓሪስ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ጐንዴክ ፡ ለወር ፡ ያህል ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ። በአፍሪቃ ፡ የሕግና ፡ የፖለቲካ ፡ (አገዛዝ) ፡ ጉዳይ ፡ የሚዋሐድበት ፡ መንገድ ፡ የሚያስረዱ ፡ ንግግሮች ፡ ከማ

ድረጋቸውም ፡ በላይ ፡ እዚህ ፡ በቆዩበት ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥት ፡ ሕግ ፡ (Public Law) መግቢያ ፡ ኮርስ ፡ ሲያስተምሩ ፡ ነበሩ ። የኒዮርክ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ፕሮፌሰርና ፡ በኢትዮጵያ ፡ እ. ኤ. አ. ከ፲፱፻፵፱ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ ሆነው ፡ የነበሩት ፡ ጋርትሰን ፡ ለማንም ፡ ክፍት ፡ የሆኑ ፡ ከሁለተኛ ፡ ዓለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ በተደረጉት ፡ መሻሻሎች ፡ ሕግ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ቦታ ፡ እንደያዘ ፡ የሚያስረዱ ፡ ብዙ ፡ ንግግሮች ፡ አድርገዋል ። የተፍትስ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ፕሮፌሰሮች ፡ ሚገሀርና ፡ ሊ ፡ እንዲሁም ፡ የኢንዲያና ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ፋቱሮስ ፡ ሕግና ፡ ዕድገት ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ ሴሚናር ፡ አድርገዋል ። ታንዛኒያ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ የቀድሞ ፡ የሕግ ፡ ዲን ፡ የነበሩት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ያሽ ፡ ጋይ ፡ በምሥራቅ ፡ አፍሪቃ ፡ የመንግሥት ፡ ሕግ ፡ (East African Public Law) በቅርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ዕድገቶች ፡ ላይ ፡ የፋክልቲ ፡ መምህራን ፡ ሴሚናር ፡ ሰጥተዋል ። የአላባማ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሲንገር ፡ (ዱሮ ፡ የኛ ፡ ፋክልቲ ፡ አባል ፡ የነበሩት ፡) በኢትዮጵያ ፡ ስለሕግ ፡ መለወጥ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ዝንባሌዎችን ፡ እንዳላቸው ፡ የሚያሳይ ፡ መረጃዎች ፡ አቅርበዋል። የአፕሳላ፡ዩኒቨርስቲ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሳንድስትሮም ፡ (የቀድሞ ፡ የኛ ፡ ፋክልቲ ፡ አባል ፡ የነበሩት) ፡ ሁለት ፡ የመንግሥት ፡ ሕግ (Public Law) ሴሚናሮች ፡ ሰጥተዋል ፤ ሚስተር ፡ እልያል ፡ በታንዛኒያ ፡ ስለመሬት ፡ ይዞታ ፡ ማሻሻል ፡ የሚገጥሙትን ፡ ችግሮች ፡ በብዙ ፡ በኩል፡ በመመልከት ፡ ንግግር ፡ አድርገዋል ። አቶ ፡ ጳውሎስም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለመሬት ፡ ይዞታ ፡ ተናግረዋል ። ሚስተር ፡ አብሬዝ ፡ ለደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሽያጭ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ችግር ፡ (Arms Sale) ለመወጣት ፡ የአፍሪቃ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚችል ፡ አስረድተዋል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ በያመቱ ፡ ከፋክልቲያችን ፡ ውጭ ፡ የመጡ ፡ በጣም ፡ የታወቁ ፡ ተናጋሪዎችን ፡ ለመስማት ፡ ዕድል ፡ ብናገኝም ፡ እኔ ፡ እንደሚሰማኝ ፡ ከሆነ ፡ የዘንድሮ ፡ ተከታታይ ፡ ንግግሮች ፡ የተለየ ፡ ችሎታ ፡ የሚያሳዩ ፡ ናቸው ።

<u>የፋክልቲው ፡ የገንዘብ ፡ አቋምና ፡ አስተዳደሩ ።</u>

በዚህ ፡ መግለጫዬ ፡ ተከታዩ ፡ አጠቃላይ ፡ ክፍል ፡ የሚመለከተው ፡ "የተለመዱ ፡ ክንውኖችና ፡ ድርጊቶች ፡" ሲሆን ፡ አንድ ፡ ለማለት ፡ የፈለግሁት ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ዓመቱን ፡ ለመጨረስ ፡ ያስቻለን ፡ ጥሩ ፡ የገንዘብ ፡ አቋም ፡ "የተለመደ" ፡ ነገር ፡ ነበር ፤ ድንገት ፡ ፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ በማይረዳበት ፡ ነገሮች ፡ ምክንያት ፡ የተነሱትን ፡ ችግሮች ፡ ለማቃለል ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ጥረት ፡ ሳደርግ ፡ ከድሮው ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ አጥፍቻለሁ ።

በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የተገኙ ፡ ውጤቶች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ። ድሮ ፡ በፎርድ፡ ፋውንዴሽን ፡ እርዳታ ፡ ይካሄድ ፡ የነበረው ፡ ለእትምና ፡ ለዋና ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይወጣ ፡ የነበረው ፡ ገንዘብ ፡ አሁን ፡ ከዩኒቨርስቲ ፡ በሚገኘው ፡ ባጀት ፡ ይካሄዳል ፤ ሁለተኛው፡ ውጤት ፤ ፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ ለዚህ ፡ ዓመት ፡ ጥናት ፡ ማካሄጃ ፡ ገንዘብ ፡ ለመስጠት ፡ ከመስማማቱም ፡ ሌላ ፡ ለሁለት ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ መምህራን ፡ መቅጠሪያና ፡ ጥናት፡ ማካሄጃ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ እ. አ. አ. ከ፲፱፻፸፩ ፡ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ እኛ ፡ ያስፈልገናል ፡ ብለን ፡ በጠየቅነው ፡ መሠረት ፡ እንደሚሰጥ ፡ አረጋግጦልናል ።

ከፎርድ ፡ ፋውንዴሽን ፡ የሚሰጠው ፡ እርዳታ ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. በርግጥ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ተረጋግጦ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የገንዘብና ፡ የመከተያ ፡ ደንብ ፡ (Policy) እንደገና ፡ በማመዛዘን ፡ (በመገመት) ፡ ለዩኒቨርስቲው ፡ እንዲሁም ፡ ለሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ከሚሰጠው ፡ እርዳታ ፡ ከመቶ ፡ አምሳ ፡ (50%) መቀነሱ ፡ ታውቋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በመጨረሻ ፡ ላይ ፡ ሳናመሰግነው ፡

የማናልፍው ፡ ለሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ያስፈልጋል ፡ ብለን ፡ ለምናስበው ፡ የሚሆነውን ፡ ያህል ፡ ለመስጠት ፡ በማቀዱ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ዞር ፡ ብለን ፡ ማየት ፤ ያለብን ፡ ባለን ፡ ገንዘብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ለማስገኘት ፡ የሚገፋፋ ፡ ጥረት ፡ መደረግ ፡ እንዳለበት ፡ ነው ፤ ይህንንም ፡ ማለት ፡ ከውጭ ፡ የሚገኘው ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ ዝቅ ፡ እያለ፡ መሄዱ ፡ የማይቀር ፡ ዕዳ ፡ ስለሆነ ፡ ለዚሁ ፡ ችግር ፡ መፍትሔ ፡ የሚሆን ፡ ፕሮግራም፡ ማዘጋጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

በአስተዳደር ፡ በኩል ፡ ሚስተር ፡ ጆን ፡ ኤዲ ፡ በረዳት ፡ ዲንነት ፡ መምጣታቸው ፡ በጣም ፡ ዕድለኞች ፡ አድርጎናል ። ባለፈው ፡ ዓመት ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ ረዳት ፡ ዲናችን ፡ ከመሄዳቸው ፡ የተነሣ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ አዲሱ ፡ ረዳት ፡ ዲን ፡ በትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የድሮ ፡ ቦታቸውን ፡ እንዲይዙ፡ ለማድረግ፡ ችለዋል ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ዩኒቨርስቲውን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ለቀው ፡ ለነበሩት ፡ ተማሪዎች ፡ በሁለተኛ ፡ የክረምት ፡ ማሟያ ፡ ትምህርት ፡ ፈንታ ፡ ሌላ ፡ መፍትሔ ፡ በማግኘት፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ብቻ ፡ ክረምት ፡ እንደይማሩ ፡ ለማድረግ ፡ የቻሉት ፡ እርሳቸው ፡ ነበሩ ። ሚስስ ፡ ኒሲይ ፡ አኬሎ ፡ የታንዛኒያ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ምሩቅ ፡ የሆኑት ፡ በሕግ ፡ ነክና ፡ በአስተዳደር ፡ በኩል ፡ ችሎታ ፡ በሞላበት ፡ አኳኋን ፡ እርዳታ፡ ሲሰጡ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ኬኒያ ፡ በመሄዳቸው ፡ ሐዘን ፡ ተሰምቶናል ፡

## ሰ. <u>የተለመዱ ፡ ክንውኖችና ፡ ድርጊቶች ፡</u>

በፋክልቲው ፡ የተለመደ ፡ መሻሻል ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ከምናስበው ፡ ጋር ፡ እያይዘን፡ መጥቀስ ፡ የሚገባን ፡ ከድርጊቶቹ ፡ ውስጥ ፡ ዕድገትን ፡ የሚያሳዩ ፡ ነገሮች ፡ አሉ ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ። ለቀው ፡ በሄዱት ፡ መምህራን ፡ ተጀምሮ ፡ ከፍጻሜ ፡ ያልደረሱ ፡ ውጥኖች ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የራሳቸውን ፡ የምርምር ፡ ጥናት ፡ የሚጠቀሙበትን ፡ ጊዜ ፡ የሚከፋፈል ፡ ቢሆንም ፡ በአዲሶች ፡ መምህራን ፡ እንዲጨረሹ ፡ ማድረግ ፡ ከማስፈለጉ ፡ የተነሣ ፡ ልያጋጥሙን ፡ ከሚችሉ ፡ ችግሮች ፡ መኖራቸውን ፡ አምና ፡ አጥብቄ ፡ ማስገንዘቤ፡ የሚታወስ ፡ ነው ። ከመምህራን ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ መስዋዕትነት ፡ ማስፈለጉ ፡ ጥርጥር ፡ የሌለው ፡ ቢሆንም ፡ ሸክሙ ፡ ከባድ ፡ እንደሆነ ፡ ይቆያል ።

### <u>ምርምርና ፡ እትም ።</u>

ረዳት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ካተሪን ፡ አ ፡ ዶኞባንና ፡ በሳቸው ፡ የሚመራው ፡ የምርምርና ፡ እትም ፡ ኮሚቴ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ፓልና ፡ ክላፍም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ዕድገት ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ የጻፉትን ፡ ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፡ መጽሐፍ ፡ ለአታሚዎች ፡ ሰጥተዋል ፡ (ልከዋል) ። ይህ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲጠበቅ ፡ የቆየው ፡ መጽሐፍ ፡ በብዙ ፡ አዘጋጆችና ፡ ረዳቶች ፡ የተዘጋጀ ፡ ሲሆን ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ረዳት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ካተሪን ፡ ሲመሩ ፡ በውጭ ፡ በኩል ፡ ጄምስ ፡ ፖል ፡ ሥራው ፡ እንዲፈጸም ፡ አበረታተዋል ። ጄምስ ፡ ፖል ፡ ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መታተም ፡ ጉጉታቸው ፡ የሚወለድ ፡ ልጅ ፡ እንደሚጠብቅ ፡ አባት ፡ ነበር ። ሁላችንም ፡ በዚህ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ተደስተናል ። የረዳት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ካተሪን ፡ ኮሚቴ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቺቺኖቪች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነት ፡ ሕግ ፡ የጻፉትን ፡ መጽሐፍ ፡ ከማሳተሙም ፡ በላይ ፡ የተጠቃለሉትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ (በኢዊንግ ፡ ዋና ፡ አዘጋጅ) ፡ እትም ፡ ጀምሯል ። ይህ ፡ ከአንድ ፡ ሺ ፡ ገጽ ፡ በላይ ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ክፍሉ ፡ የያዘው ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ በፋኩልቲው ፡ ውስጥ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ታላቅ፡ጥረት የተደረገበት ፡ ነው ። ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ፋኩልቲው ፡ የዚህን ፡ እትም ፡ በፍጥነት ፡ መውጣት ፡ ያስታውቅ ፡ ነበር ። ግን ፡ እነዚህ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በሥራው ፡ ቶሎ ፡

መውጣት ፡ የመንግትን ፡ እንጂ ፡ በእውነት ፡ የሥራው ፡ መፈጸምን ፡ ሁኔታ፡እያመለከ ትም ፡ ነበር ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ የምንገልጸው ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ የመጀመሪያው፡ ገጽ ፡ እርግት ፡ ተጠቃሎ ፡ ለማየት ፡ መብቃታችንን ፡ ነው ።

ቀድሞ ፡ የዚህ ፡ ፋኩልቲ ፡ አባል ፡ የነበሩት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቫንደርሊንደን ፡ በፓ ሪስ ፡ ስለ ፡ ዘመናዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ጽፈው ፡ አሳትመ ዋል ።

ሁለት ፡ ተጨማሪ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ እትሞች ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ወጥተዋል ። እነሱም ፡ ቮልዩም ፡ ፮ ፡ ቁጥር ፡ ፪ና ፡ ቮልዩም ፡ ፯ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ናቸው ። ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎች ፡ በሚከተሉት ፡ ርእሶች ፡ ተጽፈዋል ። በኢትዮጵያ ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የፍቺ ፡ ሁኔታ ፡ (በበክስትሮም) ፤ በኢትዮጵያ ፡ የበታች ፡ ፍርድ/ቤቶች ፡ አሠራር ፡ (ጌራቲ) ፤ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ (ምርሀውስ) ፤ እና የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በወጣት ፡ ጥፋተኞች ፡ ላይ ፡ (ፊሸር) ።

ባለፉት ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ ሚስተር፡ ዚግሙንት ፡ፕላተር ፡ ለዚህ ፡ መጽሔት ፡ መውጣትና ፡ ለተማሪ ፡ አዘጋጆዎች ፡ ሥራ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ኃላፊነት ፡ ሲሰሩ ፡ ቆይተዋል ። ከኢትዮጵያ ፡ መሄዳቸው ፡ ስለሆነ ፡ ልባዊ ፡ ምስጋናችንን ፡ እናቀርባለን ። የሳቸው ፡ መለየት ፡ በመጽሔት ፡ አወጣጥ ፡ ፕሮግራማችን ፡ ጉድለት ፡ መተው ፡ አይቀ ርምና ፡ ፋኩልቲ ፡ ይህን ፡ ጉድለት ፡ እንዴት ፡ ለማሟላት ፡ እንደሚችል ፡ በጥብቅ ፡ ማሰብ ፡ ይገባዋል ።

<u>የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህራን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ።</u>

በተወሰነላቸው ፡ መጠን ፡ ከማስተማራቸውም ፡ ሌላ ፡ መምህራን ፡ በብዙ ፡ ሌላ ፡ ጠቃሚ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ተሰማርተው ፡ ነበር ።

አቢዩ ፡ ገለታ ፡— ተጠይቀው ፡ ለዩኒቨርሲቲው ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ምክትል፡ ፕሬዚዳንት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ጠቀስ ፡ ምክሮች ፡ ሰጥተዋል ። እንዲሁም ፡ ለኢትዮ ጵያ ፡ ንብረት ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ የሚሆን ፡ መጽሐፍ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ምርመራቸውን ፡ ቀጥለዋል ።

ፍራንስ ፡ ሲ ፡ ባላንስ ፡— በስርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ትልቅ ፡ ጥናት ፡ ያጠናቀቀው ፡ የሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፤ በ፫ ቮልዩም ፡ የተከፈለ ፡ ለሕግና ፡ ኤኮኖሚ ፡ መሻሻል ፡ ትምህርት ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚረዳ ፡ መጽሐፍ ፡ አዘጋጅተዋል ፡ በሲራኩስ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሊተታም ፡ የታቀደውን ፡ ዛምቢያና ፡ የምሥራቅ ፡ አፍሪካ ፡ አንድነት ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ የተጻፈ ፡ ጽሑፍ ፡ አጠናቀዋል ፤ የአካዳሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ አባል ።

ብርሃኔ ፡ ገብሬይ ፡— የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የዲፕሎማና ፡ የሰርቲፊኬት ፡ ፕሮግራም፡ ዲሬክተር ፡ (ገለጻ ፡ እታች ፡ ተመልከት) ፤ የዩኒቨርሲቲው ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባዔ ፡ (ፋኩልቲ ፡ ካውንስል) አባል ፤ የዩኒቨርሲቲው ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፤ የምክትል ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ የደሞዝና ፡ ተመሳሳይ ፡ ጥቅሞች ፡ ጊዜያዊ ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፤ ስለ ፡ ታክስ ፡ ሕግ ፡ ምርምራቸውን ፡ ቀጥለዋል ።

ጃክስ ፡ ቢሮ ፡— የአማርኛ ፤ የፈረንሳይኛና ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ሌክሲኮን ፡ ፕሮጀ ክትን ፡ የመጀመሪያ ፡ (የቀዳሚ) ፡ ዝግጅት ፡ ሥራ ፡ አጠናቀቁ ።

ጆን ፡ ኤዲ ፡— ረዳት ፡ ዲን ሰፋ ፡ ላለ ፡ ለፋኩልቲው ፡ አስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ ኃላፊ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ ዋናው ፡ ዲን ፡ በሌሉ ፡ ጊዜ ፡ ጊዜያዊ ፡ ዲን ፡ ሆነው ፡ ያገለግላሉ ፤ በብዙ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ አመራር ፡ ክፍሎች ፡ አባል ፤ የዲኑ ፡ ጉባዔ ፡ (ዲንስ ፡ ካውንስል) ፤ የሊቃውንት ፡ ጉባዔና ፡ ወደ ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ የሚገቡትን ፡ አዲስ ፡ ተማሪዎች ፡ የመቀበልን ፡ ሁኔታ ፡ የሚቆጣጠረው ፡ ቦርድ ፡ አባል ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ኮሚቴዎች ፡ አባል ፡ ምሳሌ ፡ አካዳሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ የተማሪዎች ፡ ግንኙነት ፡ ኮሚቴ ፤ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የመጽሐፍ ፡ መራጭ ፡ ኮሚቴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሐላፊነት ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ ጽሑፍ ፡ ምርምራቸውን ፡ ቀጥለዋል ። እንዲሁም ፡ ለግጼታ ፡ ትምህርት ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎችን ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ጆርጅ ፡ ክርቺኖቪች ፡— የኢትዮጵያ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኃላፊነት ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ አሳትመዋል ። እንዲሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ በዩኒቨር ሲቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ጊዜ ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ ጽሑፍ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ከመላካ ቸውም ፡ በላይ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ልጅነት ፡ ማስረጃ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲታተም ፡ ልከዋል ፡ (በኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ ኢንስቲቱት) ። ስለ ፡ ውል ፡ አመሠራረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምርምራቸውን ፡ ቀጥለዋል ። ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽ ሔት ፡ ሕጋዊ ፡ ምርምር ፡ (ኩዊዝ) የሚያስፈልጋቸውን ፡ ጥያቄዎች ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ለሕግ ፡ መጽሔት ፡ ስለ ፡ ምስራቅ ፡ አፍሪካ ፡ የተዘጋጁትን ፡ ጽሑፎች ፡ ከቬርሄልስት ፡ ጋር ፡ በመመርመር ፡ ላይ ፡ ናቸው ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኪሣራ ፡ ሕግ ፡ ጥናት ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ሕግ ፡ በመጻፍ ፡ ላይ ናቸው ። ለማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎችን ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነት ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ ጋር ፡ በማነጻጸር ፡ (ኮምፐራቲቭ ፡ ቶርት) ፡ በሚል ፡ ርዕስና ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራና ፡ አላግባብ ፡ መበልጸግ ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ ጽሑፎች ፡ ጽፈው ፡ አጠና ቀዋ ። በብዙ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲና ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሚቴዎች ፡ አባል ፡ ናቸው ። ለኢ ንተርናሽናል ፡ (ለአንድ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ አካዳሚ) ፡ አካዳሚ ፡ እፍ ፡ ኮምፐራቲቭ ፡ ሎው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ገለጻ ፡ አድርገዋል ። እንዲሁም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ግንኙነቶችን ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ አድርገዋል ።

ፍራንዝ ፡ ላንግ — የአገር ፡ ውስጥ ፡ አገዛዝ ፡ (ሎካል ፡ ገቨርመንት) ፡ አመሠራ ረት ፡ ሕጋዊና ፡ ፖለቲካዊ ፡ አቋሙ ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ አንድ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ አፍ ሪካ ፡ ፎርም ፡ በተባለ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ አሳትመዋል ። ሳንድትሮም ፡ ስለኛ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቴ ፡ የጻፉትን ፡ ጽሑፍ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ እንዲታተም ፡ ከእንግሊዝኛ ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ ቋንቋ ፡ ተርጉመዋል ። እንዲሁም ፡ ዳኞችና ፡ ዳኛ ፡ ነክ ፡ የሆነ ፡ ሥል ጣን ፡ ያላቸው ፡ በመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ (ኤክዚኩቲቭ) ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ያላ ቸው ፡ መድን ፡ (ጥበቃ) ፡ በአፍሪካ ፡ በሚል ፡ ርዕስ ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ መጻፍ ፡ ጀምረ ዋል ። ለአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ የሚጠቅሙ ፡ የሕግ ፡ ጽሑፎች ፡ ከጀርመን ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ተርጉመዋል ።

ሮበርት ፡ ሜሊን ፡— ለማስረጃ ፡ ትምህርት ፡ የሚረዱ ፡ ጽሑፎችን ፡ መሰብሰብ ፡ ጀምረዋል ፤ እንዲሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እርዳታ ፡ ክሊኒክ ፡ እንዲመሠረት ፡ እር ዳታ ፡ አድርገዋል ፤ እንዲሁም ፡ ከመንግሥቱ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋር ፡ ገና ፡ ያልጸደቀው ፡ የማስረጃ ፡ ሕግ ፡ ሊሻሻል ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ተነጋግረዋል ።

ጆን ፡ ሜሲንግ ፡— ለአንድ ፡ ትምህርት ፡ (ትራንዝናሽናል ፡ ትራንዛክሽንስ)፡ ማስ ተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ በ፩ ፡ ቮልዩም ፡ አዘጋጅተው ፡ ጨርሰዋል ፤ ለተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ትምህርት ፡ የሚሆን ፡ ፪ ፡ ቮልዩም ፡ ማስተማሪያ ፡ አጠናቀዋል ። የዩኒቨርሲ

ቲው ፡ ሊቃውንት ፡ ጉባዔ ፡ አባል ፡ (ጀን ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ከፋኩልቴው ፡ መለየታቸው ፡ ስለሆነ ፡ በሁላችንም ፡ ትልቅ ፡ ቅሬታን ፡ ይፈጥራል ። ሁሉ ፡ መምህር ፡ እንደሳቸው ፡ የምስተማሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ በብዛትና ፡ በሥራው ፡ ደንበኛነት ፡ ቢያወጣ ፡ በጣም ፡ መሻሻል ፡ እናረግ ፡ ነበር ። በሊቃውንቱ ፡ ጉባዔም ፡ (ፋኩልቲ ፡ ካውንስል)፡ የሳቸው ፡ መለየት ፡ ትልቅ ፡ ባዶ ፡ ቦታ ፡ ይተዋል ፡ ምክንያቱም ፡ በዚህ ፡ ጉባዔ ፡ ውስጥ ፡ የሥራቸው ፡ ትክክለኛነትና ፡ የማግባባት ቸሎታቸው ፡ እንዱ ፡ አድርጓቸው ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ነው ።

አን ፡ ማሪ ፡ ጃኮሚ ፡ ሚሴት ፡— ስምምነት ፡ (ትሪቲ) ፡ ሕግ ፡ በካናዳ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በፓሪስ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ አሳትመዋል ። እንዲሁም ፡ አምቡድስማን ፡ በአፍሪካ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ አንድ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ በሬቪው ፡ ጀኔራል ፡ውስጥ፡ ጽፈዋል ፤ የአፍሪካ ፡ የሕግ ፡ እድገት ፡ ድርጅት ፡ ለአፍሪካ ፡ ኤኮኖሚክ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ጥበቃ ፡ ጉባኤ ፡ ጓድ ፡ አባል ፤ የጂሰፕ ፡ ዓለም ፡ አቀፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የክርክር ፡ ውድድር ፡ (ሙት ፡ ኮርት) ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ረድተዋል ። እንዲሁም ፡ ብዙ ፡ ንግግሮች ፡ በሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዲዘጋጁ ፡ አድርገዋል ። የአፍሪካ ፡ ኢንስቲቱቶች ፡ (አፍሪካን ፡ ኢንስቲቱትስ) ፡ ለሚል ፡ ትምህርት ፡ ማስተማሪያ ፡ ጽሑፎች ፡ አዘጋጅተዋል ።

ካተሪን ፡ አ ፡ ደኖቫን — የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የምርምርና ፡ እትም ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሲሆኑ ፡ ይህ ፡ ኮሚቴ ፡ ሁለት ፡ መጻሕፍት ፡ ከማሳተሙም ፡ በላይ ፡ ሁለት ፡ ሌላ ፡ መጽሔት ፡ ወደ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ልኳል ። እንዲሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ እንዲታተም ፡ ረድቷል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎች ፡ አዘጋጅ ። ለግለ ፡ ሰብ ፡ ሕግ ፡ (ፕራይቬት ፡ ሎው) ፡ መግቢያ ፡ ትምህርት ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎችን ፡ አዘጋጅተዋል ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍና ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ። በፋኩልቲው ፡ የሚገኙ ፡ የብዙ ፡ ኮሚቴዎችና ፡ የአካዳሚክ ፡ ኮሚሲዮን ፡ አባል ።

ዚግሙንት ፡ ፕላተር ፡— ሁለት ፡ እትሞች ፡ ያሳተመውና ፡ ፫ኛውን ፡ ለአታሚ ዎች ፡ የላከው ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ሊቀ ፡ መንበር ። የአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ድርጅት፡ ለአፍሪካ ፡ ኤኮኖሚክ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ጥበቃ ፡ ጉባዔ ፡ ጓድ ፡ አባል፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ አፍሪቃ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አቋም ፡ (አፍሪካን ፡ ኮንስ ቲቱሽናሊዝም) ፡ ለጉባዔው ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ጽፈው ፡ አቅርበዋል ። የቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ የመጽሔት ፡ ቦርድ ፡ አባልና ፡ ለአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ (አፍሪካን ፡ ሎው ፡ ሪፖርትስ) ፡ ዜና ፡ አቀባይ ናቸው ።

ሮን ፡ እስክላር ፡— የጂሱፕ ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ ፍ/ቤት ፡ የተማሪዎች ፡ ክርክር ፡ ውድድር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቱ ፡ በኩል ፡ ዋና ፡ አዘጋጅ ፤ የብዙ ፡ የፋኩልቲው ፡ ኮሚ ቴዎች ፡ የአካዳሚክ ፡ ኮሚሽን ፡ ጭምር ፡ አባል ፤ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በፈቃድና ፡ በሀሳብ ፡ ስለሚደረግ ፡ ጥፋት ፡ አንድ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ መጻፉ ቸውን ፡ ቀጥለዋል ። እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ተመሳሳይ ፡ ጽሑፍ ፡ መጻፍ ፡ ጀምረዋል፤ ተጨማሪ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎችን ፡ ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ማዘ ጋጀታቸውን ፡ ቀጥለዋል ።

ቢ. ጂ. ቴነሪ ፡— ከግንቦት ፡ ፳፭ ፡ እስከ ፡ ግንቦት ፡ ፳፱ ፡ እ. ኤ. አ. "ጠበቃና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በኢትዮጵያ" በመባል ፡ የተዘጋጀው ፡ ጉባዔ ፡ አዘጋጅና ፡ አቀነባባሪ፡ በዚህ ፡ ጉባዔ ፡ ላይ ፡ ታላላቅ ፡ በፍርድ ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ የመንግሥት ፡

ባለሥልጣኖች ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ አባሎችና ፡ የታወቁ ፡ የግል ፡ ጠበቆች ፡ ተገኝተዋል ። በኢትዮጵያ ፡ የሕብረ ፡ ሥራ ፡ ሕግ ፡ ለመጻፍ ፡ ምርምራቸውን ፡ ጀምረዋል ፤ የኢትዮጵያ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ግንኙነት ፡ ምርምር ፡ ማኅበር ፡ አቋቋሚ ፡ (ፋውንደር) አባል ፤ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ኮሚቴና ፡ የተማሪዎች ፡ ግንኙነት ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ።

ቲየሪ ፡ ጂ. ቨርሄልስት ፡— የአፍሪካ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ድርጅት ፡ ዲሬክተር ፤ እንዲሁም ፡ ለአፍሪካ ፡ ኤኮኖሚክ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ጥበቃ ፡ ጉባዔ ፡ እርዳታ ፡ ይሰጣሉ ፡ (እላይ ፡ ገለጻ ፡ ተመልከት) ፤ በሩዋንዳ ፡ ላልተማሩ ፡ የፍርድ ፡ ሠራተኞች ፡ ትምህርት ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ፡ ምክር ፡ ይሰጣሉ ፤ ስለ ፡ ሕግና ፡ እድገት ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲው ፡ ብዙ ፡ ንግግሮች ፡ አዘጋጅተዋል ፤ ለእድገት ፡ ሕግ ፡ ሁለት ፡ የምርምር ፡ ጽሑፎችን ፡ አሳትመዋል ፡ (ሉቤን ፡ ዩኒቨርሲቲና ፡ ቦስተን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት) ፤ ለመሬት ፡ ይዞታ ፡ ማሻሚያ ፡ ትምህርት ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎችን ፡ ማዘጋጀት ፡ ጀምረዋል ።

ፒተር ፡ ዊንሺፕ ፡— ሕግና ፡ የኤኮኖሚ ፡ ቁጥጥር ፡ የሚል ፡ አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ጀምረው ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎችን ፡ አጠናቀዋል ፤ ስለንግድ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍና ፡ እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚጠቅሙ ፡ ጽሑፎችን ፡ ማዘጋጀት ፡ ጀምረዋል ። የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ኮሚቴ ፡ አባልና ፡ የመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ተማሪዎች ፡ የምርምር ፡ ጽሑፍ ፡ ፕሮግራም ፡ ዋና ፡ አቀናባሪ ፤ የፋኩልቲውና ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡" ኮሚቴ ፡ አባል ።

ዮሐንስ ፡ ሕሩይ ፡— በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚያደርገውን ፡ ምርምር ፡ ቀጥሏል ።

## በውጭ ፡ አገር ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ የፋኩልቲው ፡ መምህራን ።

ፋሲል ፡ ናሆም ፡— ለኤል ፡ ኤል ፡ ኤም ፡ ዲግሪ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጥናት ፡ በየል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ አጠናቀው ፡ ከአማካሪዎቻቸውም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ ውጤት ፡ አግኝተዋል ።

ወርቁ ፡ ተፈራ ፡— ለኤል ፡ ኤል ፡ ኤም ፡ ዲግሪ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጥናት ፡ በኖርዝ ፡ ዌስተርን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አጠናቀው ፡ ከአማካሪዎቻቸው ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ ውጤት ፡ አግኝተዋል ።

ስመረአብ ፡ ሚካኤል ፡— በብሩስልስ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ በውል ፡ ሕግ ፡ ለመጻፍ ፡ ምርምራቸውን ፡ ቀጥለዋል ፤ ይህ ፡ መልእክት ፡ በሚጻፍበት ፡ ጊዜ ፡ ከአማካሪው ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መግለጫ ፡ አልደረሰኝም ።

## ከዲግሪ ፡ በታች ፡ ስለሚያስገኘው ፡ የማታ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራም ።

ዶክተር ፡ ብርሃኔ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ አዳዲስ ፡ ኮርሶች ፡ ከፍተዋል ። ከ፪፻ ፡ እጩዎች ፡ ውስጥ ፡ ለ፪፻ ፡ (200) ተማሪዎች ፡ አዲስ ፡ የዲፕሎማ ፡ ፕሮግራም ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ከማድረጋቸውም ፡ በላይ ፡ ሁለት ፡ ልዩ ፡ ፈተናዎች ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ (ቴስቲንግ ፡ ሴንተር ፡) የሚሰጡ ፡ እንዲዘጋጁ ፡ አድርገዋል ።

እንዲሁም ፡ ለ፵ ፡ (40) የሚሆኑ ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ኮርስ ፡ ከፍተዋል ። ለሁለቱም ፡ ኮርሶች ፡ አዲስ ፡ የማስተማሪያ ፡ ዘዴዎች ፡ ከመዘጋጀታቸውም ፡ በላይ ፡ ፰ (8) እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ አስተማሪዎች ፡ ተመርጠዋል ።

በፈተናው ፡ ክፍል ፡ ከተዘጋጁት ፡ ፈተናዎች ፡ የተገኘው ፡ አስደናቂ ፡ ውጤት ፡ የእጩዎችን ፡ የትምህርት ፡ አቅዋምና ፡ ደረጃ ፡ የሚለየው ፡ ነበር ። የፈተናው ፡ ውጤት ምርመራ ፡ እንደሚያሳየው ፡ ተፈታኞቹ ፡ (እጩዎች) ፡ በ፫ ታላላቅ ፡ ክፍሎች ፡ (ግሩፕስ) ፡ ተከፍለዋል ፡ ፲፪ኛ ፡ ክፍል ፡ ትምህርት ፡ ደረጃ ፡ የደረሱ ፤ እዚህ ፡ ደረጃ ፡ ያልደረሱ ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ ሰርቲፊኬት ፡ ፕሮግራም ፡ ተካፍለው ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ያገኙና ፡ ከሁለቱም ፡ ያልሆኑ ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ ነክ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ (ከ፲ ዓመት ፡ በላይ) የተሰማሩ ፡ ፈተናዎቹ ፡ በአማርኛ ፡ ሲሆኑ ፡ በመሠረቱ ፡ የተፈታኞቹን ፡ የማንበብና ፡ ነገሩን ፡ የማወቅ ፡ ችሎታቸውን ፡ ለማጣራት ፡ የተዘጋጁ ፡ ነበሩ ። አንባቢ ፡ እንደ ፡ መሆንህ ፡ መጠን ፡ የትኛው ፡ ወገን ፡ (ግሩፕ) ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ እንዳመጣ ፡ ለመገመት ፡ ትችላለህን? በግለ–ሰብ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ መኖሩ ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው ። ግን ፡ እንደ ፡ ክፍላቸው ፡ ዓይነት ፡ ችሎታቸውም ፡ የተለያየ ፡ ነበር ። በማዕርጋቸውም ፡ መጀመሪያ ፡ የሆኑት ፡ ያው ፡ እላይ ፡ እንደተዘረዘረው ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ ፈተና ፡ ከዲግሪ ፡ በታች ፡ ላለው ፡ ፕሮግራም ፡ የትምህርት ፡ መስጫ ፡ ጽሑፎች ፡ ብዛትና ፡ዓይነት ፡ እንዲሁም ፡ ሥርዓቱ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ መሆን ፡ እንደሚገባው ፡ ለማወቅ ፡ ጠቃሚ ፡ ስለሚሆን ፡ ወደፊት ፡ በ(ቴስቲንግ ፡ ሴንተር ፡) እውቀትና ፡ እርዳታ ፡ ለመጠቀም ፡ አስበናል ።

የ፲፱፻፸—፸፩ ፡ እ. ኤ. አ. የማታ ፡ ትምህርት ፡ ክፍል ፡ አስተማሪዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ። አቶ ፡ አባቢያ ፡ አባጀቢር ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፤ ክቡር ፡ አቶ፡መሐመድ፡ አብዱራሕማን ፡ የጡረታ ፡ ኮሚሽነር ፤ ዶክትር ፡ አሰፋ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ በንግድ ፡ ኢንዱስትሪና ፡ ቱሪዝም ፡ ሚኒስቴር ፡ ሕግ ፡ አማካሪ ፤ አቶ ፡ አሰፋ ፡ ሊበን ፡ ከፍተኛ ፍርድ፡ቤት ፡ ዳኛ ፤ ዶክተር ፡ በረከተ ፡ አብ ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሕግ ፡ አማካሪ ፤ አቶ ፡ ስዑል ፡ ሚካኤል ፡ ረዳት ፡ ዓቃቤ ፡ ሕግ ፤ ሻለቃ ፡ ሺመልስ ፡ መታፈሪያ ፡ መከላከያ ፡ ሚኒስቴር ፡ አማካሪ ፤ አቶ ፡ ዘገየ ፡ አሰፋው ፡ መሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ ሕግ ፡ አማካሪ ።

## <u>የሥርዓተ ፡ ትምህርትና ፡ የአካዳሚክ ፡ ደረጃ ፡ (ይዞታ) ።</u>

የሚስተር ፡ ፍራንክ ፡ ባላንስ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ኮሚቴ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ ብዙ ፡ ክርክርና ፡ ምክክር ፡ በኋላ ፡ በሚያዝያ ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ፋኩልቲው ፡ እንዲነጋገርበት ፡ አቅርቧል ። ኮሚቴው ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ሀሳቦችን ፡ አፍልቋል ፡ ግን ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ በነበረው ፡ ውዝግብ ፡ ምክንያትና ፡ እንዲሁም ፡ በተደረጉት ፡ በብዙ ፡ አስቸኳይ ፡ ስብሰባዎች ፡ በቀረበው ፡ ሀሳብ ፡ መነጋገሩ ፡ ለሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ በመተላለፉ ፡ ሁላችንም ፡ በጣም ፡ እናዝናለን ። በቀረቡት ፡ ሐሳቦች ፡ ላይ ፡ ሳይነጋገሩ ፡ ሚስተር ፡ ፍራንክ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለቀው፡ መሄዳቸው ፡ ስለሆነ ፡ ቅሬታ ፡ ይሰማናል ።

በመስከረም ፡ ፲፱፻፸፩ ፡ ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.) ስለ ፡ ፋኩልቲው ፡ አቅዋም ፡ አስተያየት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ያሽ ፡ ጋይ ፡ ያቀርባሉ ። እኚህ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቀድሞ ፡ በታንዛኒያ ፡ ውስጥ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ ዲን ፡ ነበሩ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በዬል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ት/ቤት ፡ የምርምር ፡ አባል ፡ (ሪሰርች ፡ ፌሎው) ፡ ናቸው ። እኔም ፡ እዚህ ፡ እንዲመጡ ፡ የጠየቅኋቸው ፡ መልካም ፡ ሀሳብ ፡ በማፍለቅና ፡ በተጠራጣሪ ፡ አስትሳሰባቸው ፡

የታወቁ ፡ በመሆናቸውና ፡ እንዲሁም ፡ በለራሳችን ፡ አቅዋም ፡ አስተያየትና ፡ እንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ችሎታ ፡ ባለው ፡ የታወቀ ፡ የውጭ ፡ ሰው ፡ ያስፈልገናል ፡ ብዬ ፡ ስለማምን ፡ ነው ።

በውጭ ፡ አገር ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ ለሚገኙ ፡ መምህራን ፡ ጽፌንላቸው ፡ ረጅምና ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ መልሶችን ፡ አግኝተናል ። ስለ ፡ ጠበቃና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተደርጎ ፡ በነበረው ፡ ውይይት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ መሻሻል ፡ ብዙ ፡ ሀሳቦችን ፡ ከመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ከግል ፡ ጠበቆች ፡ አግኝተናል ። ወደፊትም ፡ ከነዚሁ ፡ ጋር ፡ ውይይታችንን ፡ እንቀጥላለን ። እንዲሁም ፡ በንግግሮቹ ፡ ውስጥ ፡ የአሁንና ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ እንዲካፈሉ ፡ ለማድረግ ፡ አስበናል ። መልካምና ፡ ፍሬያማ ፡ ዓመት ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

እኔ ፡ በጣም ፡ የምጨነቀው ፡ እያንዳንዱ ፡ ትምህርት ፡ (ኮርስ ፡) ስለሚሰጠው ፡ እውቀት ፡ ሳይሆን —ይህም ፡ በጥንቃቄ ፡ መታሰብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነው ፡ ግን ፡ እያንዳንዱ ፡ ምሩቅ ፡ ጠበቃ ፡ (የሕግ ፡ ሰው ፡) ሊኖረው ፡ ስለሚገባው ፡ ችሎታ ፡ ነው ። እንደሚሰማኝ ፡ ይህን ፡ በደንቡ ፡ አላስብንበትም ። እነዚህን ፡ ችሎታዎች ፡ ሰፋ ፡ አድርጌ ፡ እገልጻቸዋለሁ ። እነሱም ፡ የሚከተሉትን ፡ በውስጣቸው ፡ ይይዛሉ ፡ ሰው ፡ የሚያጋጥመውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ችግሮች ፡ መለየት ፤ አስፈላጊዎቹን ፡ የሕብረ ፡ ሰብና ፡ ሌላ ፡ ምክንያቶች ፡ መነጠል ፤ የልዩ ፡ ልዩ ፡ መፍትሔ ፡ ውጤቶችን ፡ ማቀናበርና ፡ ችግሩን ፡ ለመቋቋም ፡ የሚችልበትን ፡ ሁኔታ ፡ ማቅረብ ። ተማሪውም ፡ በቃልም ፡ ሆነ ፡ በጽሑፍ ፡ የመከራከር ፡ ችሎታውን ፡ ለማዳበር ፡ እንዲችል ፡ መደረግ ፡ አለበት ። በተለይም ፡ ተማሪው ፡ ከታሰበው ፡ ዓላማ ፡ ጋር ፡ የሚሆኑ ፡ ከሕግ ፡ ውስጥ ፡ ቅያሪዎችን ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ሕጎችን ፡ ለማርቀቅ ፡ መቻል ፡ አለበት ።

በዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ከማጠቃለያው ፡ ፈተና ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ እያንዳንዱ ፡ መምህር ፡ ችሎታ ፡ ለተማሪዎች ፡ በምስጢር ፡ የተዘጋጀ ፡ ጥያቄ ፡ አቅርቤ ፡ ነበር ፡ የተማሪዎቹ ፡ መልስ ፡ እውነተኛን ፡ ስሜት ፡ የሚገልጽና ፡ መልካም ፡ ነበር ። አስተማሪዎቹም ፡ በነዚህ ፡ በተሰነዘሩት ፡ እነሱን ፡ በማሞገስና ፡ እንዲሁም ፡ ስለነሱ ፡ በተሰጡት ፡ የጥርጣሬ ፡ አስተያየቶች ፡ በመስከረም ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ስነጋገር ፡ ይጠቀማሉ ብዬ ፡ አምናለሁ ። በጠቅላላው ፡ ብዙዎቹ ፡ መልሶች ፡ (ሁሉም ፡ ሳይሆኑ) ፡ መምህራኑን ፡ የሚያመሰግኑ ፡ ነበሩ ። ግን ፡ መልሶቹ ፡ ለአስተማሪዎቹ ፡ ስለዚህም ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ይጠቀማሉ ።

በዚህ ፡ ዓመት ፡ በየፋኩልቲው ፡ የሚገኙ ፡ ተማሪዎች ፡ በ፪ኛ ፡ ሴሚስተር ፡ መጨረሻ ፡ ሳምንቶች ፡ ላይ ፡ ትምህርት ፡ በማቋረጣቸው ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓመት ፡ ክፍሎች ፡ ተዘግተው ፡ ነበር ። በየቦታው ፡ የምዘዋወር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ እንደመሆኔ ፡ መጠን ፡ ተማሪዎቹ ፡ ትምህርት ፡ በማቋረጥና ፡ ሌላም ፡ ተመሳሳይ ፡ ሥራዎችን ፡ በመሥራት ፡ የሚያገኙትን ፡ የፖለቲካ ፡ ጥቅም ፡ ልገምት ፡ አልችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ በሱዳን ፤ በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፤ በዛምቢያና ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያስተማርኩ ፡ መምህር ፡ እንደመሆኔ ፡ መጠን ፡ የትምህርት ፡ ደርጃ ፡ (አካዳሚክ ፡ ስታንዳርድ) ፡ በዚህ ፡ ተደጋጋሚ ፡ ትምህርት ፡ ማቋረጥ ፡ ምክንያት ፡ እንደሚጎዳ ፡ ጥርጥር ፡ የለኝም ። በተለይ ፡ የዚህ ፡ ችግር ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ መንፈሴን ፡ አውኮታል ። ይኸውም ፡ በብዙ ፡ ተማሪዎች ፡ ዘንድ ፡ ሊታመን ፡ የሚፈለገው ፡ አንድ ፡ አስተማሪ ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ከተናገረ ፡ የተማሪዎችን ፡ የፖለቲካ ፡ ሥራ ፡ እንደ ሰደበ ፡ ይቆጠራል ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ነው ። በአንድ ፡ በኩል ፡ ልክ ፡ ናቸው ። የዩኒቨርሲቲ ፡ መምህራን ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ደርጃን ፡ መጠበቅ ፡ በማውራት ፡ ተማሪዎች፡

ክጥናት ፡ ሌላ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ እንዳይካፈሉ ፡ በማድረግ ፡ ጥረዋል ። ይህ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ግን ፡ በተማሪዎችም ፡ በኩል ፡ ከፍተኛ ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ መጠበቅን ፡ ጥቅም ፡ መካድ ፡ ተመሳሳይ ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ መውደቅ ፡ ነው ። የወደፊቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ቢያመጣ ፡ የተማሩ ፡ ዶክተሮች ፤ መሐንዲሶች ፤ ጠበቆች ፤ የሕብረ ፡ ሰቡ ፡ መሐንዲሶች ፡ እንደሚባሉት ፡ በጣም ፡ ማስፈለጋቸው ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ከእያንዳንዱ ፡ ውዝግብ ፡ በኋላ ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ ደርጃ ፡ ዝቅ ፡ ቢልና ፡ ጥሩ ፡ ውጤቶች ፡ በቀላሉ ፡ ቢሰጡ ፡ የኛ ፡ ተማሪዎች ፡ ለአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ ሊፈጽሙ ፡ አይችሉም ። የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ተማሪዎቹን፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ምሩቃን ፡ እንዲሆኑ ፡ ስለሚፈልግ ፡ የትምህርቱን ፡ አሰጣጥ ፡ ደርጃ ፡ ተማሪዎቹ ፡ እነሱ ፡ ወደፊት ፡ ለሚያገለግሏቸው ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ይፈልጋል ።

የኛ ፡ ተማሪዎች ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ፍ/ቤት ፡ የተማሪዎች ፡ ክርክር ፡ ውድድር ፡ ላይ ፡ ያስገኙት ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ የኛ ፡ ፋኩልቲ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ደረጃ ፡ ሊደርስ ፡ እንደሚችል ፡ የሚያሳይ ፡ አንድ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። "የኛ" ፡ ያልኩበትም ፡ ምክንያት ፡ ሁሉም ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ከፍተኛ ፡ ውጤት ፡ የማግኘት ፡ ችሎታ ፡ ስላላቸው ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ ጐበዝ ፡ አስተማሪዎች ፤ ጐበዝ ፡ ተማሪዎችና ፡ (እነዚህ ፡ አሉን ፡) ከባድ ፡ ሥራ ፡ የመሥራት ፡ ችሎታ ፡ ያስፈልጉታል ። ከባድ ፡ ሥራ ፡ ለማንኛውም ፡ ሰው ፡ በተመሳሳይ ፡ ደረጃ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ተማሪዎች ፡ ጭምር ፡ ጥልቅና ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ የመሥራት ፡ ችሎታን ፡ መገንባት፡ አለባቸው ። እንደሚሰማኝ ፡ መምህራንና ፡ ተማሪዎች ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ከባድ ፡ ሥራን ፡ የመሥራት ፡ ችሎታ ፡ ማነጽ ፡ በሚቻልበት ፡ መንገድ ፡ መስማማት ፡ አለባቸው ፡ ምክንያቱም ፡ አንዱ ፡ ሀሳብን ፡ ማቀናበርና ፡ ቶሎ ፡ መያዝ ፡ ችሎታዎች ፡ ከባድ ፡ ሥራን ፡ መልመድ ፡ ራሱ ፡ አንድ ፡ ችሎታ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።